| የእውነታ መረጃ ወረቀት | 2026 |
|---|---|

# የAurora Ave ፕሮጀክት

## የፕሮጀክት ዳራ

Aurora Ave N (State Route 99) በሲያትል ውስጥ፣ ሰዎችን ወደ ቤታቸው፣ ንግድ ሥራዎቻቸው፣ አገልግሎቶች እና ከስራዎቻቸው ጋር የሚያገናኝ እጅግ በጣም ከተጨናነቁ መንገዶች አንዱ ነው። ይህ ኮሪደር የክልሉን ከፍተኛ የተሳፋሪ ቁጥር ያለውን የአውቶቡስ መስመር፣ RapidRide E መስመርን የሚያገለግል ሲሆን፣ ለጭነት ማመላለሻም ወሳኝ ነው። እንዲሁም ለSDOT ከፍተኛ የደህንነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፣ ምክንያቱም በተለይም በእግር ለሚጓዙ ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ከባድ ጉዳት እና ገዳይ አደጋዎች ይከሰቱበታል።

የSDOT የAurora Ave ፕሮጀክት አሁን ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ ማሻሻያዎችን እያደረገ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ጊዜ ለAurora Ave N የወደፊት አዲስ የረጅም ጊዜ ራዕይ እየነደፈ ነው። እነዚህ ለውጦች ደህንነትን ለማሻሻል እና ሁሉም ተጓዦች በቀላሉ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የታለሙ ናቸው።

## የAURORA AVE ፕሮጀክት ኮሪደር እቅድ ጥናት

በ2022 ከአጋር ድርጅቶቻችን ጋር በመሆን ኮሪደር የማቀዱን ጥናት ጀምረናል። ግባችን ለAurora Ave N በማህበረሰብ የሚመራ አዲስ የንድፍ እይታ መፍጠር ነው።

የማቀድ ምዕራፉ እስከ 2028 ድረስ እንደሚቆይ ይጠበቃል። ይህ እቅድ በኮሪደሩ ውስጥ ለሚደረጉ የወደፊት መዋዕለ-ንዋዮች መመሪያ ይሆናል።

የኮሪደር ማቀድ ጥናቱ ግቦች የሚከተሉት ናቸው፦

- ለAurora Ave N ለእያንዳንዱ ሰው ሁሉ ደህንነት፣ መንቀሳቀሻ እና ተደራሽነት ላይ ያተኮረ **አዲስ የንድፍ እይታ ማደራጀት**
- ፍትሃዊ በሆነ የተሳትፎ ሂደት በAurora Ave N ዙሪያ ያሉ **ሰዎችን የተለያዩ ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ማስገባት**
- **በኮሪደሩ ላይ ያሉ የማመላለሻ እና የደህንነት ተግዳሮቶችን መፍታት**
- **ሊሆኑ የሚችሉ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ማሻሻያዎችን እና ግንኙነቶችን ለይቶ ማወቅ**
- **እንደ ሀብቶች ግኝት** የኮሪደር ማሻሻያዎችን ለመገንባት ስትራቴጂ ማደራጀት

እስከ 2028 መጨረሻ ድረስ፣ የሚከተሉትን ለማድረግ እንጠብቃለን፦:

- በ2024 ጋራናቸውን የማህበረሰብ ሀሳቦች ረቂቅ ማጣራት
- ወደ ንድፈ ዕቅድ፣ የተፈጥሮ አካባቢ ግምገማ፣ እና አተገባበር ለመሸጋገር ያለውን አማራጭ መምረጥ




*የAurora Ave ፕሮጀክት ከRoy St እስከ N 145th St ይዘልቃል። ካርታው በሁለት ክፍሎች የተከፈለ ነው - ከGreen Lake እና ከGreen Lake በስተደቡብ - ምክንያቱም የመንገዱ ስፋት ከግሪን ሌክ በስተሰሜን ይጠባል።*



*መግለጫ፦ የማህበረሰብ አባላት በ2024 ውስጥ ለAurora Ave N የንድፍ ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ አስተያየት ይሰጣሉ*

## ከእርስዎ ጋር እንዴት እንደምንሰራ

ከእርስዎ መስማት እንፈልጋለን! እርስዎ እና የእርስዎ ጎረቤቶች ግብረ መልስ ማጋራት የምትችሉባቸው እና በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ ተሳታፊ የምትሆኑባቸው ብዙ መንገዶች አሉ፦

- **የእርስዎን ሀሳብ ይላኩልን፡፡** በ **aurorastudy@seattle.gov** ወይም በ **(206) 905-3620** ሊያገኙን ይችላሉ
- **ከእኛ ጋር በራስ-ብቅ ባይ ዝግጅት፣ ገለጻ ወይም የማህበረሰብ ዝግጅት ላይ ይገኙ፡፡.** የፕሮጀክቱ ቡድን መረጃን በዝግጅቶች ላይ እና ከማህበረሰብ ቡድኖች ጋር ለማጋራት በአካባቢው ይገኛል፡፡ **የዝግጅቶቻችንን የተዘመነ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ለፕሮጀክት ኢሜሎቻችን በፕሮጀክቱ ድህረ-ገጽ ላይ ይመዝገቡ →**
- **በማህበረሰብ አማካሪ ቡድናችን በኩል፡፡** በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ፣ በAurora Ave N አቅራቢያ ከሚኖሩ፣ ከሚሰሩ፣ ከሚማሩ፣ ከሚያመልኩ ወይም ጊዜ ከሚያሳልፉ የተለያዩ ሰዎች ጋር እንሰራለን፡፡ የፍትሃዊ እኩልነት የፕሮጀክት ውሳኔዎችን ለመምራት እንዲረዳ በማመላለሻ እቅዶች፣ ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች እና የንድፍ አማራጮች ላይ ግብዓት ይሰጣሉ፡፡

## እርስዎ ምን መጠበቅ እንደሚችሉ

በኮሪደሩ ላይ የአጭር ጊዜ ማሻሻያዎችን ቀድሞውኑ አስተውለው ይሆናል፡፡እነዚህን ለውጦች እያደረግን ያለነው አሁን በAurora Ave ላይ የሕዝብ ማመላለሻ ለሚወስዱ፣ በእግር ለሚሄዱ፣ በብስክሌት ለሚጋልቡ እና ለሚያንከባልሉ ተጠቃሚዎች ደህንነትን እና ዘመናዊ መንቀሳቀሻ ለማሻሻል ነው፡፡



*የሰራተኛ ቡድኖች ለአዳዲስ የእግረኛ መሻገሪያዎች እና የመሻገሪያ ምልክቶች ለመዘጋጀት በAurora Ave N እና N 137th St ላይ አስፋልት እያነጠፉ*

**ለአሁኑ ወቅት እና ለታቀዱ ማሻሻያዎች፣ የተሳትፎ እድሎች፣ እና ሌሎችም የAurora Ave N ፕሮጀክት ድህረ-ገጽን ለመጎብኘት የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ፦**

**የፕሮጀክት መረጃ እና መገናኛ**
aurorastudy@seattle.gov
(206) 905-3620
www.seattle.gov/transportation/auroraproject